# ስለ ዲኤችኤችኤስ

የጤና እና ሰብዓዊ አገልግሎቶች (ዲኤችኤችኤስ) አላማ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎችን ጤና እና ደህንነት ለማጎልበት እና ለማረጋገጥ እንዲሁም የግለሰብ እና ቤተሰባዊ ጥንካሬ እና በራስ መተዳደርን ለመገንባት ነው።

## *መመሪያ ነጥቦች*

- በደንበኞቻችን እና ማህበረሰቡ ጥንካሬን የሚያበለጽጉ አገልግሎቶችን እናቀርባለን።
- ለማህበረሰባችን ተለዋዋጭ ፍላጎቶች ምላሽ እንሰጣለን።
- ተወዳዳሪ፣ የደንበኛ አገልግሎት የሚሰጡ ሰራተኞችን እንቀጥራለን እንዲሁም እናጸናለን።
- ለአገልግሎቶች አቅርቦት የ የተሳሳተ በር የለም የተባለ አካሄድ ስራ ላይ እናውላለን።
- አገልግሎቶችን ለሚፈልጉ ሁሉ ከፍተኛ ጥራት ያለውን የደንበኛ አገልግሎት  ለመስጠት ቁርጠኛ ነን፤ እንዲሁም ሰራተኞቻችን አክብሮት፣ ባለሙያነት፣ ጊዜ አክባሪነትን እና ሚዛናዊነትን እንዲያንጸባርቁ በሃላፊነት እኒይዛለን።
- የሰራተኞቻችንን ክህሎት እና ቁርጠኝነት ዋጋ እንሰጣለን፤ ስለዚህም በቂ ድጋፍ፣ ሃብቶች እና ስልጠና በማቅረብ ደንበኞቻችንን በደንብ እንዲያገለግሉ እናደርጋለን።

*ታማኝነት-ደንበኛ አገልግሎት-ድርሻ-ተጠያቂነት*



PACS

DHHS
MONTGOMERY COUNTY

# እቅድ፣ ተጠያቂነት እና ደንበኛ አገልግሎት

## የአገልግሎት ዝርዝሮች




PACS


የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንት
እቅድ፣ ተጠያቂነት እና ደንበኛ አገልግሎት

401 Hungerford Drive
Rockville, MD 20850
(240)-777-1098

DHHS.PACS@MontgomeryCountyMD.gov
www.montgomerycountymd.gov/HHS/PACS/PACS.html


ሞንትጎመሪ ካውንቲ፣ ሜሪላንድ
የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንት
እቅድ፣ ተጠያቂነት እና ደንበኛ አገልግሎት

# እቅድ፣ ተጠያቂነት እና ደንበኛ አገልግሎት

እቅድ፣ ተጠያቂነት እና ደንበኛ አገልግሎት (ፒኤሲኤስ) በዳይሬክተሩ ቢሮ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን የዲፓርትመንቱን አላማ የሚደግፈውም የፕሮግራም አፈጻጸም መለኪያ፣ የመረጃ ስብሰባ እና አመራር፣ ግምገማ እና ትንታኔ፣ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የዲኤችኤችኤስ ፕሮግራሞችን አገልግሎት አቅርቦት እቅድ እና ፖሊሲ ትንታኔ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የዲኤችኤችኤስ ፕሮግራሞችን አገልግሎት አቅርቦት ያጠቃለሉ የአገልግሎቶችን ዝርዝር በማቅረብ ነው።

## ፒኤሲኤስ ዋና የስራ ክልሉን የሚያከናውነው በሚከተሉት ነው፥

- የደንበኞችን ውጤት የሚገልጽ ትርጉም ያልው የፕሮግራም መለኪያዎችን በማጎልበት እና በማጥራት፤
- አላማ ያላቸውን የአገልግሎት ጥራት ምርመራዎችን እና የማህበረሰብ ምርመራዎችን ስራ ላይ በማዋል፥
- በጥልቅ የቡድን ስብሰባ ሂደት አማካይነት የአገልግሎትን ውህደት መደገፍ፥
- ለአገልግሎት ቦታዎች፣ ፕሮግራሞች፣ እና ውስብስብ የህብረተሰብ አገልግሎት ሲስተሞች በአስፈላጊው የብቃት መለኪያ ላይ የአቅም ግንባታ፥
- የመጠቁ እና የተቀናጁ ቴክኖሎጂ፣ የመረጃ ሲስተሞች፣ እና የትንተና መሳሪያዎችን በመጠቀም፥
- ከሌሎች የመንግስት ኤጀንሲዎች፣ የማህበረሰብ አጋሮች፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና የምርምር ማዕከላት ጋር ውጤታማ አጋርነትን በማጎልበት

## ትንተና እና የብቃት መለኪያ

ትርጉም ያላቸው የብቃት መለኪያዎችን ማጎልበት እና ትንተናን በመጠቀም የተቀናጁ አገልግሎቶች ጥራት እና ፍትሓዊነትን ለማረጋገጥ በየጊዜው ሪፓርት ማድረግ

የጥራት ፕሮግራም መንደፊያ 7  አካላትን በመጠቀም፣ ፒኤሲኤስ፣ ከፕሮግራም ሰራተኞች ጋር በመስራት፣ ሃብቶች ከንድፈ ሃሳብ ወደ ተግባር እንዴት እንደሚሄዱ ያለውን የሎጂክ እና መለኪያዎች በመከተል፣ አገልግሎቶች ምን ያህል በብዛት እና በጥራት እንደቀረቡ እና በደንበኞች ላይ ያመጡትን ለውጥ አስተዳዳሪዎች እንዲያውቁ በማድረግ ነው። እነዚህ መለኪያዎች ሰዎችን፣ አሰራሮችን እና ፓሊሲን ወደሚያሳውቀው ዲኤችኤችኤስ ሄድላይን መለኪያዎች ይቀየራሉ።

## የአገልግሎት ጥራት ግምገማዎች

በደረጃ የተቀመጡ የአገልግሎት ጥራት ግምገማዎች (ኪውኤስአር) የሚያቀርበው በጊዜ የተገለጹ የጥራት ግምገማዎች እና የደንበኞችን ሁኔታ እና ደህንነት ትንተና እንዲሁም የአገልግሎት ሲስተሙ ጥራት፣ ተከታታይነት፣ እና ውጤታማነት ነው። ወሳኝ ነጥቦች ላይ ብቃትን በመለካት፣ ፒኤሲኤስ የሚረዳው ሰራተኞች፣ የአሰራር ልምዶች፣ እና በአጠቃላይ ፕሮግራሞች ግለሰቦችን እና ቤተሰቦችን ለማገልገል እንዴት በሲስተም እየሰሩ እንደሆነ ነው። የነዚህ ግምገማዎች ውጤት የሚያረጋግጡት ከፍ ያለ ጥቅም የሚያስገኙትን አገልግሎቶች ደንበኞች ማግኘታቸውን ነው።

## የማህበረሰብ ግምገማዎች

የማህበረሰብ ግምገማ በደረጃ የተቀመጠ የራስ ግምገማ ፕሮግራም ሂደት ሲሆን በቀጣዩም የሚካሄድ ነጻ ግምገማ እውቀት ባላቸው የሰለጠኑ የማህበረሰብ የበጎ ፈቃድ ፓነል ይካሄዳል። ግምገማው ፒኤሲኤስን የሚያሳውቀው የፕሮግራሙ አገልግሎት አቅርቦት ከዲፓርትመንቱ አላማ እና ግቦች ጋር ምን ያህል እንደተጣጣሙ ነው። ውጤቶቹም የጥንካሬ ቦታዎችን እና መሻሻል ያለባቸውን ቦታዎች ስራ ላይ ሊውል የሚችል ግብ ላይ ያነጣጠሩ አስተያየቶችን ለዲኤችኤችኤስ አመራር እና ሰራተኞች እንዲገመግሙት በመጨረሻው ሪፓርት ላይ ያቀርባሉ።



## ጥልቀት ያለው የቡድን ስብሰባ ማስተባበር

ጥልቀት ያላቸው የቡድን ስብሰባዎች (አይቲኤም) የጤና እና ሰብዓዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት መሳሪያዎች ሲሆኑ የሚያገለግሉትም የደንበኞችን ፈታኝ የአገልግሎት ፍላጎቶችን ለመመለስ በተጠራቀመ የአገልግሎት መቀናጀትን በማዋል ነው። አይቲኤም ደንበኞችን፣ የተለያዩ የአገልግሎት ቦታዎች ጉዳይ መሪዎችን እና በደንበኞች እንክብካቤ የሚሳተፉ ሌላ የውስጥ እና የውጭ አቅራቢዎችን አንድ ላይ በማምጣት የደንበኞችን ጤና እና ደህንነት ለማሻሻል በተቀናጁ ስብሰባዎች እና ስምምነት በተደረገባቸው የድርጊት እቅዶች በሁሉም የአገልግሎት ቦታዎች ላይ ይሰራል። ፒኤሲኤስ የስብሰባ ማስተባበርን ያረጋግጣል እንዲሁም የአይቲኤም ሂደት እና ውጤቶችን ይቆጣጠራል።

## ተግባር ማጎልበቻ ቡድን

የተግባር ማጎልበቻ ቡድን (ፒኢቲ) የተቀናጀ ሂደት ሲሆን የሚያረጋግጠውም የዲኤችኤችኤስ ፕሮግራሞች ኢንቨስትመንቱን እየተጠቀሙ እንደሆነና የመጠቁ የተቀናጀ ቴክኖሎጂ፣ የመረጃ ሲስተሞች እና የትንተና መሳሪያዎች በመጠቀም አስተዳደሩን ስለ ፕሮግራሙ አሰራር ልምድ እንዲያውቅ ያደርጋሉ። ከተለያዩ ዲፓርትመንቶች የተውጣጣው ቡድን ከአስተዳዳሪዎች እና ከሰራተኞች ጋር በመስራት ውጤታማ የአሰራር ልምድ ሂደቶችን፣ የደንበኛ መዝገቦችን፣ የድርጅቱን ቴክኖሎጂ መፍትሔዎች (ኤሌክትሮኒክ የጤና መዝገቦች እና ኤሌክትሮኒክ የተቀናጀ የጉዳይ አመራር) መረጃ አገባብ አጠቃቀሞችን፣ የአስተዳደር ሪፖርት ማድረጊያ እና የብቃት መለኪያዎችን እንዲሁም ውጤቶችን ይመረምራል።